# የፅዳት ደህንነት መጠበቂያ ምክሮች ወረቀት

በፅዳት ኢንዱስት ላይ ከስራ ጋር የተያያዙ ጉዳቶችን ለመከላከል ተከታታይ የጤናና ደህንነት ምክሮች



**ጁን 2019** **ቁጥር 1, ቅፅ 1**

## የአደጋ ማስጠንቀቅያ ምስልና ፅሑፎችን ያውቋቸዋል?

**ምስልና ፅሑፎቹ እርስዎ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ በሚችሉ ኬሚካሎች ላይ እንዲለጠፉ ሕግ ያስገድዳል፡፡**

በመከተል የተመለከቱት የአደጋ ማስጠንቀቅያ ምስልና ፅሑፎች የፅዳት ስራ ላይ የተለመዱ ምልክቶች ናቸው፡፡

እያንዳንዱ ምስልና ፅሑፍ ሊያጋጥም የሚችል የጤና አደጋ ያብራራል እና ጉዳት ለማስቀረት ጠቃሚ ምክሮችን ይሰጣል፡፡

### አደጋና ጉዳት

ካንሰር ሊያስከትል ይችላል፡፡

የሳንባ መቆጣትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

የመውለድ አቅም ወይም ፅንስ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

የሰውነት ክፍሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

የዘረመል መዛባት ሊያስከትል ይችላል፡፡

**ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ምርቶች ምሳሌ:**

- Aquaclean፡፡
- Tom Shirley Wood to Wood፡፡



### መከላከያ እርምጃ

ከተዋጠና ወደ ሳንባ ከገባ ሊገድል ይችላል፡፡

ምርቱን በባዶ እጅዎ አይንኩት፡፡

የፅሑፍ ስርአቱን ይወቁ ይረዱ፡፡

ምርቱን በተሰጠው መመርያ መሰረት ይደባልቁ፡፡

ኬኒካሎችን በፍፁም አይደባልቁ፡፡

ኬሚካሎችን ከአየር ላይ ይልቅ ቀረብ አድርገው ይርጩ፡፡

የእጅ ጓንት፣ ሽርጥ፣ የአፍንጫ መከላከያ ይጠቀሙ፡፡

Washington State Department of Labor & Industries

ጥናቱን በተመለከተ ተጨማሪ ለማወቅ ወደ SHARP ይደውሉ/አጭር
የፅሑፍ መልእክት ይላኩ/ኢሜይል ያድርጉ

360-819-7908 ▪ 1-888-667-4277 ▪ JanitorStudy@Lni.wa.gov

SHARP Safety & Health Assessment & Research for Prevention

SHARP ሪፖርት ቁጥር: 102-02-2019

## አደጋና ጉዳት

በተወሰነ ሁኔታ የሚነዱ ወይም እሳት የሚጭሩ ጋዞች፣ ኤሮሶሎች፣ ፈሳሾች ወይም ጠጣር ነገሮች፡፡

ለትንሽ ሙቀት፣ ፍትግያ፣ ሃይል ወይም ሌላ ኬሚካል ከተጋለጠ እሳት ሊፈጥር ወይም ሊፈነዳ ይችላል፡፡

ከሌሎች ኬሚካሎች ጋር አደገኛ ነገር ሊፈጥር ይችላል፡፡



## መከላከያ እርምጃዎች

ከሙቀት/ብልጭታ/እሳት/የሚሞቅ ቦታ ያርቁት እና በቂ አየር በሚዘዋወርበት ስፍራ ላይ ያስቀምጡት፡፡

ምርቱ ወደ አየር እንዳይለቀቅ ይጠንቀቁ፡፡

መከላከያ የእጅ ጓንት፣ መከላከያ ልብስ፣ የአይን መከላከያ እና/ወይም የፊት መከላከያ ያጥልቁ፡፡

አቧራ ወይም ጭስ ወደ ውስጥ አያስገቡ፡፡

ከስሩ በኋላ ክንድዎን፣ እጅዎንና ፊትዎን ይታጠቡ፡፡

ከሚነዱ ወይም እሳት ከሚያስነሱ ፈሳሽ ነገሮች፣ ጋዞች ወይም ጠጣር ነገሮች ጋር በፍጹም አይደባልቁ፡፡